**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት** (ኢሕአፓ ወክንድ)
**Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)**


ጥቅምት 10 2006 ዓ.ም

# ኢትዮጵያዊ ወደ ሁለተኛ ዜግነት ወጣቱን ለዘመናዊ ባርነት

ወያኔ አገራችን ኢትዮጵያን ከፖለቲካ መልከዓ ምድር ለመፋቅ የዓምስት ዓመቱን የፋሺስት ወራሪ በሚያስንቅ የጥላቻ ፈረስ ሲጋልብ 22 የጨለማ ዓመታትን አስቆጠረ። ባዕዳንና ምርጥ ቡችሎቻቸው የመጀመሪያው፣ ሕዝባችን ሁለተኛ ዜጋ የሆነበት፣ ወጣቱ በሀገሩ ሰርቶ የመኖር እድሉ ክርችም ብሎ ተዘግቶበት በባዕድ አገሮች ለዘመናዊ ባርነት ሰለባ ሆኗል። በዚህ ዓመት ወክ ፍሪ ፋውንዴሽን ( Walk Free Foundation) የሚባለው ግብረሰናይ ተቋም ባወጣው ዓለም ዓቀፍ የባርነት ማጣቀሻ ( Global Slavery Index) የጥናት መረጃ መሠረት፣ ኢትዮጵያ በዘመናዊ ባርነት ስር በወደቁ ዜጎች ብዛት ከሚታወቁት 162 አገሮች ውስጥ 12 ኛውን ቦታ ይዛለች። በጥናቱ መሠረት የ29.8 ሚሊዮን ከሆነው የዘመናዊ ባርነት ሰለባ ቁጥር 76 ቱን እጅ ከሚይዙት 10 አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ አንዷ ሆናለች።

ወያኔ ትውልድ ገዳይ በሆነ የትምህርት ፖሊሲው አገሪቱን አምራች ከሆነው የህብረተሰብ ክፍል ለማምከን ደፋ ቀና ማለቱ ብቻ ሳይሆን በቀጥታና በተዘዋዋሪ ለዘመናዊ ባርነት የወጣት ጉልበት አቅራቢ ሆኗል። ገና ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ህፃናት ለፆታ ባርነት የሚጋዙበት፣ በቃጠሎ በረሃና ቅዝቃዜው እንደ ስለት በሚቆርጥ ውቅያኖስ ሰምጠው የሚያልቁበት፣ በዘረኛና ቀናተኛ አለቆቻቸው ቃላት ሊገልፀው የማይችል ግብረ ሰቆቃ የሚዳረጉበት፣ ወጣት አትዮጵያዊት ሴት በአደባባይ እየተንተተች ስትሰቃይ ብሎም አንቀው ሲያጠፏት የፋሺቱ ወያኔ ኤምባሲ “ታዲያ እኛ አገሪቱን ያዝን እንጅ ኢትዮጵያዊ አይደለን” የሚል መልእክት በአረመኔነት እያስተላለፈ ለዜጎቿ ያለው ጥላቻ እንዳለ ሆኖ፣ ዋናው ምክንያት ግን ይህንን እኩይ ስራ በስፋት የሚያካሂደው የዘመናዊ ባርነት ንግድ ተጠቃሚ በመሆኑም ነው። ይህ አንድ ትውልድ የመምተር ወንጀል ካለፈው አረመኔ ስርዓት ስልቱን ቀየረ እንጅ በይዘቱና ጥልቀቱ የከፋ መሆኑ አነጋጋሪ አይሆንም። ታዲያ ዞሮ ዞሮ አንድ ወገናችን በቅርቡ እንዳስቀመጠው “ ለጥፋቶች ሁሉ ጥፋት ዜጎች ትልቁን ድርሻ እንወስዳለን ።ምክንያቱም ጥቂቶች ሃገር እንዲያጠፉ ብዙሃኑ ፈቅደናልና! “

## ምን መደረግ አለበት?

ወጣቱ ትውልድ የአገሪቱ የነገ ተስፋና ስርዓተ ለውጥ ለማምጣት ቀዳሚና ትልቁን ሚና የሚጫወት የህብረተሰብ አካል ለመሆኑ ያለፈው ትውልድ ልክ እንደ አርበኞች አባቶቹ ገድል ሰርቶ ታላቅ ቅርስ በተራው ለትውልድ አስተላልፏል። ወጣቱ ይህን ታሪካዊ ሃላፊነት የሚሸከምብት ምክንያት በቁጥር ካለፈው ትውልድ በተሻለ የትምህርት እድል ስለሚያገኝ፣ ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የተውጣጣ በመሆኑና የትምህርት ተቋማት ደግሞ የበለጠ የመቀራረብ እድሉን ስለሚከፍቱለት ነው።

ስለዚህ ምን መደረግ አለበት በሚለው መሪ ጥያቄ ዙሪያ **ኢሕአፓ ወክንድ (ኢ-ወክንድ)** ወጣቱ ትውልድ መብቱንና የዜግነት ክብሩን ለመጎናጸፍ እንዲችል ለማድረግና  የአገር እና የወገን ነፃነትን ለማምጣት ወያኔን ታግሎ ማቸነፍ ግድ ነው፣ በአገር ውስጥም ሆነ በመላው ዓለም ተበታትኖ (በሺዎቹ የሚቆጠረው በአሰቃቂ የባዕድ አገር ስደተኛ ማጎሪያወች ውስጥ የሚገኝና የዘረኝነት ፍዳ እየከፈለ ያለው) የሚገኘውን ወጣት በአገሩ ተከብሮ እንዲኖር የተለየና የተቀደሰ አማራጭ አለው። ይኸውም እየተደራጁ መታገል፣ እየታገሉ መደራጀት ከሚለው የእናት ፓርቲው የኢሕአፓ ጊዜ የማይሽረው የመታገያ ስልትና አላማን ከግብ ለማድረስ ትግልን በጽናት መቀጠል የሚለው መርህ  ሲሆን ተደራጅቶ በጽናት መታገልን በተግባር ለማዋል ኢ-ወክንድን እንዲቀላቀል ጥሪ ያደርጋል። ተደራጅቶ ሊያጠፋን የተነሳን ጠላት በተደራጀ ሃይል ብቻ ነው ማንበርከክ የሚቻለው።

ኢሕአፓ ወክንድ (ኢ-ወክንድ) በአረመኔው ወያኔ ላይ የሚካሄደውን ትግል አጠናክሮ ለማንቀሳቀስ በአገር ወስጥ ወጣቱን በህቡዕ በማደራጀት እንዲሁም በውጭው ዓለም በየአህጉሩ በተዋቀሩ የድርጅቱ ቻፕተሮች አማካኝነት ወጣቱን አደራጅቶ እያንቀሳቀሰ በመሆኑ ዓላማውን የሚደግፉና በትግሉ ለመሳተፍ የቆረጡ ወጣቶች በአካል በመገናኘትም ሆነ ከዚህ ገፅ ግርጌ ባለው አድራሻ በመጻፍ ወይም በመደወል የድርጅቱን ባለሞያዎች ማግኘት የሚቻል መሆኑን ማሳወቅ እንወዳለን።

ወጣቱ ዛሬም አትዮጵያን የሚታደጋት ሃይል ነው!
ኢትዮጵያ አገራችን በነፃነት ለዘላለም ትኖራለች!


Tel : 202-291-5832
e-mail: eprpylnew @gmail.com
5309 Georgia Ave. NW 2nd Fl. Washington DC 20011
Website:  www.eprpyl.com